# ገዥው ፓርቲ ተቃዋሚዎችን በቦነስ...

ፍቅረማርቆስ ከፒያሣ

ዘንድሮ የሚካሄደውን ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ በማስመልከት በፓርቲዎች መካከል እየተካሄዱ ያሉትን ክርክሮች የመመልከት እድሉ ገጥሞኛል፡፡ ሁላችንም መቼም ብዙ ነገር ታዝበናል፡፡ እኔ የታዘብኩትን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አዳመርኩና ወደ ውጤት መተንበይ ሊያደርሱኝ የሚችሉ ጠቃሚ ነጥቦችን (Empirical hypothesis) እንደሚከተለው አስቀመጥኳቸው፡፡

በዘንድሮ ክርክርና የምረጡኝ ቅስቀሳ ገዥው ፓርቲ /ኢሕአዴግ/ ተቀዋሚዎችን ቦንሷቸዋል ማለት በሚቻል ሁኔታ በልጧቸውና የምርጫውን ውጤት ለመተንበይ የሚከብድ ሆኖ አላገኘሁትም ፡፡ ለውጤት ትንበያ ይሆናሉ የምላቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ዘረዘርኳቸው፡-

የመጀመሪያውና ቀዳሚ አድርጌ የወሰድኳቸው ገዥው ፓርቲ በተግግባር ተፈትሸው በውጤት የታጀቡ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ይዞ መቅረብ ችሏል፡፡ የእነዚህ ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤታማነትን ገለልተኛ የሆኑ አካላት መስክረውላቸዋል፡፡ ለምሳሌ ለተከታታይ 6 ዓመታት የተገኘው የምጣኔ ሃብት እድገት ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲው ውጤታማ መሆኑ በተግባር ተረጋግጧል፡፡ በተቃራኒው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መያዣ መጨበጫ የሌለው፣ ከአቤቱታና ከዘለፋ ያልዘለለ ጥቃቅን ነገሮች በማግዘፍ፣ ያልተፈጠሩና የሌሉ ነገሮችን እንደተከሰቱ በማድረግ የተለያየ ቀለም በመቀባት ላይ የተጠመዱ በመሆናቸው የመራጩን ሕብረተሰብ ቀልብ መሣብ የሚችሉ አይደሉም፡፡ አብዛኞዎቹ ተቀዋሚ ፓርቲዎች ጠንካራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፈው አማራጭ የሚሉትን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የተሳናቸው ዋነኛ ምክንያት በውስጥ ችግሮቻቸው የተተበተቡ ፣ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን መተግበር የተሳናቸው፣ ወደ አመራር የሚመጡ አባሎች የግል ገናና ስምንና ስብእናን መሻት የሚወዱ በመሆናቸው ነው፡፡

በአንፃሩ ገዥው ፓርቲ ባለፉት ስድስትና ሰባት አመታት ሊታዩና ሊዳሰሱ የሚችሉ ለውጦችን ለምሳሌ፣ በመሠረተ ልማት /መንገድ ፣ መብራት፣ቴሌ/ በማህበራዊ /በትምህርትና ጤና/ እንዲሁም በመልካም አስተዳደር ዙሪያ ማንም ቀና አስተሳሰብ ያለው ሰው ሊመሰክረው የሚችል ተጨባጭ ስራዎችን ማከናወን ችሏል፡፡ ለዚህ ነው ገዥው ፓርቲ በፖሊሲዎቹና በስትራቴጂዎቹ ከተቃዋሚዎች በተሻለ መልኩ የተደራጀና የጠነከረ በመሆኑ የመራጩን ቀልብ ይገዛል ለማለት ያስደፈረኝ፡፡

በሁለተኛነት የተመለከትኩት ጉዳይ ገዥው ፓርቲ ከ 97ቱ ምርጫ ጥሩ ትምህርት ያገኘ በመሆኑ የታዩበትን ግድፈቶቹን ነቅሶ በማውጣት ከ97ቱ ምርጫ ማግስት ጀምሮ አበክሮ በመሥራት መፍትሔ ያስገኘላቸው ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ከፍተኛ የገዥው ፓርቲ አመራር በመንግሥት ኃላፊነታቸው ወደ ታችኛው ሕብረተሰብ በመዝለቅ ግለሠብ አርሶ አደሮችን፣ የተለያዩ የሙያ ማህበራትን /የመምህራን፣ ነጋዴ፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እና የሰራተኞች ወዘተ/ በማነጋገር ለችግሮቻቸው መፍትሔ በመስጠት በሕብረተሰቡና በመንግሥት መካከል ጥሩ የሚባል ግንኙነት እንዲኖር ጥሩ መሠረት ጥለዋል፡፡ ይህም ገዥው ፓርቲ በሕብረተሰቡ ውስጥ ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ዛሬ ከቀበሌ እስከ ወረዳ ፣ ዞን ክልልና በፌደራል ደረጃ ገዥው ፓርቲ ይሁንታ ያገኘና ሰፊ መሠረት ያለው ሆኗል፡፡

ከ97ቱ ምርጫ በፊት አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች "ኢሕአዴግ የሚናገር አፍ እንጂ የሚሰማ ጆሮ የለውም" አባባል ውድቅ በማድረግ የላይኛው የድርጅቱ አመራሮች ወደ ሕዝብ በመዝለቅ የልብ ትርታውን ማድመጥ በመጀመራቸው በዘንድሮው ምርጫ ኢሕአዴግ በቀላሉ የመራጩን ህብረተሰብ ቀልብ መሣብ የሚችል ይመስለኛል፡፡ በተጨማሪም ዛሬ መንግሥታዊ አገልግሎት ሰጪ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች መሠረታዊ የአሠራር ለውጥ ተግባራዊ በመሆኑ ሕብረተሰቡ በአካባቢው የተሻለ አገልግሎትን ማግኘት በመቻሉ በመንግሥት ላይ አመኔታ ጥሏል፡፡ ይህ ሌላው ለገዥው ፓርቲ ውሃ የሚቋጥር ሥራ በመራጮች ትልቅ ግምት የተሰጠው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተቃራኒው ተቀዋሚ ፓርቲዎች የአምስት አመት የቤት ሥራቸውን በአግባቡ ያከናወኑ አይመስለኝም፡፡ በመጀመሪያ ተቀዋሚዎች በ97ቱ ምርጫ ቀላል የማይባል የምክር ቤት ወንበርን በፌደራልም ሆነ በክልል ማግኘት ቢችሉም በፈጠሩት ታሪካዊ ሥህተት በሕብረተሰቡ ዘንድ ተሰሚነታቸውን ክፉኛ የሸረሸረው ይመስለኛል፡፡

በተጨማሪም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመራጮች አመኔታ ያሳጣቸዋል ብዬ የማስበው ነገር በውስጣቸው የሚታየው የፓርቲዎቹ የአወቃቀር ሁኔታ ነው ፡፡ ለዚህም ጥሩ ምሣሌ አድርጌ ማንሳት የምፈልገው መድረክ የተባለውን ፓርቲ ነው፡፡ መድረክ በውስጡ ካቀፋቸው ፓርቲዎች ገሚሱ አሃዳዊና የተማከለ አስተዳደርን የሚያቀነቅኑ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል መስማት የሚጠሉ የዜግነት ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ሁሉ ብሔራቸውን መጥቀስ የሚፈልጉ በጋራ መተሳሰብን ሳይሆን መበታተንን አዋጭ እንደሆነ በየአደባባዩ ሲናገሩ የሚደመጡ ናቸው፡፡

እንግዲህ መድረክ እንዴት አድርጎ እንደሆነ ባይታወቅም እነዚህን ሁለት ጽንፎችን በሙጫ አጣብቋቸው ኮሽ ባለ ቁጥር ቀላል የማይባሉ መስራች ፓርቲዎች በቀላሉ ከመድረክ ሲበታተኑ ታይተዋል፡፡

በእንዲህ ያለ ሁኔታ የባለፈው ቅንጅት የተሰኘው ፓርቲ የገጠመው እጣ ፈንታ መድረክ ላይ ላለመድረሱ ምን ዋስትና አለ? መድረክ አሁን ባለበት ሁኔታ እንኳንስ ከምርጫ በኋላ ላለው ሂደት ሊደርስ ይቅርና እስከ ምርጫው ድረስ እድሜ ሊኖረው ይችላል ብሎ በእርግጠኝነት መናገር ይከብዳል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ይህ በውስጣቸው የሚግመው እሳት መፈንዳት በመጀመሩ አንዳንዶች መንሸራተት ጀምሯቸዋል ፡፡ እንዲህ ያሉት ክስተቶች ተቀዋሚ ፓርቲዎች በሕብረተሰቡ ዘንድ ተአማኝነትን እንዳያገኙ ያደረጋቸው ይመስለኛል፡፡

በሶስተኝነት ሊነሣ የሚችለው የድርጅቶች አወቃቀርና የውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራራቸው ነው፡፡ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የአመሠራረት ሁኔታቸውን

ስንመለከት “ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” እንደሚባለው ምርጫ ሲደርስ የተወለዱ አለያም ከያለበት ተሰባስበው የተጣመሩ ናቸው፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስማቸውን ከዚህ በፊት ሰምተናቸው የማናውቅ፣ ጽሕፈት ቤት እንኳን የሌላቸውና የፓርቲያቸውን ሰነድ በቦርሳቸው በመያዝ በየጎዳናውና በየካፊቴሪያው የፓርቲ ሥራ የሚከውኑ ናቸው፡፡ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የተቋቋሙ ፓርቲዎች አገርን እንመራለን የሚል ብልጣብልጥ አባባላቸውን ብዙው መራጭ ሕብረተሰብ የተረዳው ይመስለኛል፡፡

የተቀዋሚ ፓርቲዎች የውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሰራራቸው ሌላው የድክመት ምንጫቸው ነው፡፡ “የጅብን ጥርስ በምን ፈራኸው ቢሉት በአጥንት” እንደሚባለው በአብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች አምባገነናዊ አሰራርን፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚል አስተሳሰብ በግልጽ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በሰጥቶ መቀበል መርሕ የማያምኑ የድርድር ፖለቲካን የማይቀበሉ በመሆናቸው የሚታዩና የሚጨበጡ እውነታዎችን መቀበል እንደ ድክመት የሚወስዱ የዜሮ ድምር ፖለቲካ አራማጆች ናቸው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡ ይህን አሰራርና አስተሳሰባቸውን ወደ ሃገር መምራት ደረጃ ይዘውት የሚመጡ ከሆነ አደገኝነቱን ማንም ሊረዳው የሚችል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮቻቸውን በወራት በሚቆጠር እድሜ በመለዋወጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን የተከተሉ ለማስመሰል ያደረጉትን ጥረት ሕብረተሰቡ ያወቀባቸው ይመሥለኛል፡፡ “የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ዳር ይማማላል” እንደሚባለው በየወራቱ የአመራሮች ለውጥ ማድረግ ዴሞክራሲያዊ አሰራር አይመስለኝም፡፡ በተቃራኒው ገዥ ፓርቲ ከአመሠራረቱ ጀምሮ የችግር አፈታት አካሄዱ እጅግ ቀጥተኛና ለሁሉም የድርጅቱ አባል እኩል መሆኑን በተግባር አሳይቷል፡፡ ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው የድርጅቱ መሥራችና ከፍተኛ አመራሮች የድርጅቱን መርሆ ወደጎን በመተዋቸው ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ተደርገው በሕግ አግባብ ተጠያቂ ሆነዋል፡፡ እንግዲህ እንዲህ ያለው አሰራር በመራጩ ሕብረተሰብ ዘንድ የፈጠረው የራሱ የሆነ መተማመኛ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በገዥው ፓርቲ በውስጥ

አሰራሩ የአመራር መተካካትን ሲተገበር የቆየ ባሕል ቢሆንም በቅርቡ ሊተገበር የታቀደው የከፍተኛ አመራር መተካካት ሂደት የፓርቲውን ዴሞክራሲያዊ አሰራር መዳበርን አመላካች በመሆኑ የመራጩን ቀልብ በቀላሉ የሚሰብ መስሎ ይታየኛል፡፡

በአራተኝነት ማንሣት የምፈልገው ነጥብ ከ97ቱ የምርጫ ሂደት ማግሥት መንግሥት በቂ ትምህርት ያገኘ በመሆኑ በአቋራጭ ወደ ስልጣን ኮርቻ መሄጃ መንገዶችና የጥፋት ፈረሰቻቸው ልጓም የተበጀላቸው ስለሆነ ለስልጣን የሚያካሂደውን ውድድር በሕጋዊ መንገድ ብቻ ስለሚያደርገው ገዥው ፓርቲ ከተቃዋሚዎች በተሻለ መልኩ እድሉ የሰፋ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ መክረው  ባፀደቁትና በኋላም በተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሆኖ የወጣው የምርጫ ስነምግባር ዘንድሮ የሚካሄደውን ምርጫ ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ የአመፃንና የነውጥ መንገድን የናደ ያደርገዋል፡፡ እንዲህ ያለው የሕግ ማእቀፍ መዘጋጀቱ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠቀሜታው የጎላ ቢሆንም ገዥው ፓርቲ የበለጠ የጎላ ያደርገዋል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ምክንያቱም የአመጽና የነውጥ መንገድ ዝግ መሆናቸው ተቃዋሚዎች በሕግ አግባብ ብቻ ወደስልጣን እንዲመጡ ስለሚያደርጋቸው ገዥው ፓርቲ ምርጫው ላይ ብቻ አተኩሮ እንዲሰራ የሚያግዘው ስለሆነ ለውጤቱ ማማር መልካም አጋጣሚ ሆኖ ይሰማኛል፡፡

በመጨረሻ በምርጫ ወቅት ለቅስቀሳ የሚውል የምጣኔ ሃብት አቅም እጅግ በጣም ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ እንደሚያሳየው መንግሥት የምርጫ ቅስቀሳ የአየር ሰዓት ወጪን ሙሉ በሙሉ ባይሸፍን ኖሮ አብዛኛው የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ምርጫው መግባት ባልተቻላቸው ነበር፡፡ በምዕራቡ አለም የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውል በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በመመደብ ነው ወደምርጫ ሲገቡ የሚታዩት፡፡  በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ያህል ገንዘብ ያስፈልጋል ማለቱ እንዳልሆነ ልብ ሊባልኝ ይገባል፤ ነገር ግን አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ቦርድ የተመደበላቸውን ገንዘብ እንኳን ለተገቢው ሥራ

ሳያውሉት ይታያሉ፡፡ በዚህ አኳያ ገዥው ፓርቲ የተሻለ የምጣኔ አቅምና የአስተዳደር ብቃት ያለው በመሆኑ የምርጫ ቅስቀሳውን በአግባቡ እየተጠቀመበት ስለሆነ ምርጫውን በድል ይወጣዋል የሚል የብዙዎች ግምት አለ፡፡

በምርጫ ሂደት ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች መራጮችን በሦስት ደረጃ ይፈርጇቸዋል፤ የመጀመሪያው ደጋፊዎቻችን የሚሏቸው ናቸው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መሃል ሰፋሪ /Swing Voter/ ጠንክሮ የሰራ፣ አሳማኝ ፖሊሲና እስትራቴጂ ማቅረብ የቻለ ፓርቲ የነዚህን መራጮች ድምጽ ማግኘት ይችላል፡፡ ሦስተኛው ደግሞ ከእነርሱ በተፃራሪ ያለውን የፖለቲካ ፓርቲ ይደግፋሉ ብለው የሚያስቧቸውን መራጮችን ነው ፡፡ ገዥው ፓርቲ ከ97ቱ ምርጫ ወዲህ የቤት ሥራውን በአግባቡ በመወጣቱ የአባላቱንና የደጋፊዎቹን ቁጥር ከሁለትና ሦስት እጥፍ በላይ ማሳደግ ችሏል፡፡ አብዛኛው መሃል ሰፋሪ የሚባለው መራጭ ዛሬ በአባልነት ወይንም በደጋፊነት ተሰልፏል፡፡ ይህ ደግሞ ለገዥው ፓርቲ ትልቅ ድል ነው፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲ አባልና ጠንካራ ደጋፊ የሚባሉት ሳይቀሩ ወደገዥው ፓርቲ መስመር እየገቡ ነው፡፡ ገዥው ፓርቲ ከእነዚህ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ድምጽ በተጨማሪ ባቀረበው በተግባር ተፈትሸው ውጤታማነታቸው በተረጋገጠ ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ የመሃል ሰፋሪን / Swing Voter/ ድምጽ የሚስብ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

እንግዲህ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች የሚያጠየነጥኑት ገዥው ፓርቲ በዘንድሮው ምርጫ አራዶች እንደሚሉት “በቦነስ” ጭምር እንደሚያሸንፋቸው በቀላሉ መተንበይ ያስችላል እላለሁ፡፡